"የማነው ?"

"መንግሥት ፡ አታየህ ? የኔ ፡ ነው !"

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ስቅቅ ፡ ብሎ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ።

"አታልቅስ ፡ እንጂ ! እንድታለቅስ ፡ አይደለም ፡ በቀበሮን ፡ ያሳየሁህ !"

"አንድ ፡ ነገር ፡ ልለምንሽ ፡ ሰብለ ።" አለ ፡ እንባና ቹንም ፡ እፍንጫውንም ፡ ከታቹን ፡ ነጥሎ ፡ በሚሄፉ ፡ እየጠራረገ ።

"ሰብለ ፡ አልባልም ! እማሆይ !"

"እሺ ፡ እማሆይ !"

"ምን ?"

"ስምት ፡ እዚህ ፡ አብረያችሁ ፡ ልሁን ፡ ቦታው ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ ይበቃል ።"

"አገርህን ፡ ትተህ ?"

"አገሬን ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ ካስለቀቀኝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜዬ ፡ ነው ፡ እንቆቅም ፡ ከምትች ፡ ሰበት ፡ አመት ፡ ሆኖኛታል ።"

"እንግዲያስ ፡ ደህና ፡ አሳብ ፡ ነው !" አለች ፡ አንገትዋን ፡ ደፍታ ፡ ካቆዩችበት ፡ ቀና ፡ አድርጋ ፡ እንባ ፡ በሞሉ ፡ አይናችዋ ፡ አንትዋን ፡ እየተመለከተች ፡ እሱም ፡ እንደሱዋ ፡ በመከራ ፡ የኖረ ፡ መሆኑ ፡ ታስባትና ፡

ጉዱ ፡ ካሳና ፡ ሰብለ ፡ በተገናኙ ፡ ባስራምስተኛው ፡ ቀን ፡ የልብ ፡ በሽታዋ ፡ ተነሳባትና ፡ እንደ ፡ ልማድዋ ፡ ወደቀች ። ነገር ፡ ግን ፡ ዳግም ፡ አልተነሳችም ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከባልዋ ፡ አጠገብ ፡ አስተኛት ፡ በሶስተኛ ፡ አመቱ ፡ እሱም ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ ተቀበረ ።



## ማረሚያ

በዚህ ፡ መጽሀፍ ፡ መቅድም ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡-

አንደኛ ፡ የፊደሎቻችንን ፡ ብዛት ፡ ለመቀነስ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ ድምጽ ፡ ካላቸው ፡ ፊደሎች ፡ አንዳንድ ፡ ብቻ ፡ እየተያዙ ፡ የቀሩት ፡ እንዲወድቁ ፡ እንዲሁም ፡ በፊደሎቻችን ፡ መጨረሻ ፡ ተመድበው ፡ የሚገኙት ፡ እንደ ፡- "ኰ - ቈ - ጐ - ኈ -" ያሉት ፡ ገደሎ ፡ ፊደሎችና ፡ ሌሎችም ፡ በመደበኛ ፡ ፊደሎች ፡ መሀል ፡ ጣልቃ ፡ እየገቡ ፡ የሚገኙት ፡ እንደ ፡- "ሟ - ሯ - ኗ - ቧ - ቯ" ያሉ ፡ ፊደሎች ፡ እንዲወድቁ ፡

ሁለተኛ ፡ ልክ ፡ እንዳነጋገራችን ፡ ባጻጻፋችንም ፡ የማንበቢያ ፡ ምልክት ፡ ቢኖረን ፡ ይልቁንም ፡ የተለያዩ ፡ ትርጉም ፡ ያላቸው ፡- እንደ ፡- "ሰውየው ፡ ሲበላ ፡ እንጀራው ፡ ሲበላ ፡" ያሉ ፡ ቃሎች ፡ ሲገጥሙን ፡ ትርጉማቸውን ፡ ወዲያውኑ ፡ ለማወቅ ፡ ስለ ምንችል ፡ ከዚያ ፡ ምልክቶቻችን ፡ "አያያዥ ፡" የሚባለው ፡ ነጥብ ፡ በሚጠበቀው ፡ ፊደል ፡ ራስ ፡ እንዲደረግ ፡ አመልክተን ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲሁ ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ አሳብ ፡ እስኪለመድ ፡ ለሰራተኛም ፡ ሆነ ፡ ለመሳሪያ ፡ ማስቸገሩ ፡ ስለማይቀር ፡ የማንበቢያው ፡ ምልክት ፡ ሊጠበቅ ፡ በሚገባቸው ፡ ፊደሎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አልተደረገም ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሊጠበቅ ፡ በማይገባቸው ፡ ፊደሎች ፡ ላይ ፡ ተደርጎ ፡ ይታያል ። እንዲሁም ፡ ይወድቁ ፡ የተባሉት ፡ ፊደሎች ፡ ተይዘው ፡ ይገኛሉ ።

ስለዚህ ፡ አንባቢዎቻችን ፡ የምንለምነው ፡ የደራሲውን ፡ አሳብ ፡ ከተረዱት ፡ ራሳቸው ፡ እያረሙ ፡ እንዲያነቡ ፡ ነው ። ሌላው ፡ የተለመደና ፡ ተራ ፡ ስህተት ፡ ማረሚያው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ተመልክቶአል ።

